አሐዱ ባንክ Ahadu Bank
ከብዙዎች ለብዙዎች
Inclusive Intermediation
ahadubank.com

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

ይቻላል
It's Possible!

ፀሐይ ኢንሹራንስ አ.ማ.
Tsehay Insurance S.C.
ፀሐይ ለሁሉም ታበራለች!!
The Sun Shines For All !!
ቦሌ ድልድይ ከብራስ ሆስፒታል ፊትለፊት
Bole Bridge, in front of Brass Hospital
Tel.+251 111 11 97 70/71 +251 111 11 98 27/97 93
Fax: +251 111 11 98 86
Website: www.tsehayinsurance.com
E-mail: marketingd@tsehayinsurance.com

አዲስ ቻምበር ADDIS CHAMBER
# ንግድና ልማት

ሐምሌ 2015 50ኛ ዓመት እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## የአዲስ ቻምበር ዋና ፀኃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም የኬንያ አምራቾች ማህበር አባላትን ተቀብለው አነጋገሩ።



በኃይል ( ኢነርጅ ) አስተዳደር ፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና መርሃ ግብር ፣ ፖሊሲ አድቮኪሲ ፣ አረንጓዴ ልማትና መሰል ዘርፎች ላይ በትብብር መስራት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ መክረዋል ።

የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተ ማርያም ስድስት አባላት ይዞ ለመጣው የኬኒያ አምራቾች ማህበር ሉዕካን ንግድ ምክር ቤታቸው እየሰራ ያለውን ስራ በተመለከተ ማብራሪያ ስጥተዋል

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## አዲስ ቻምበር የአባላት ቀንን በመጪው ሀሙስ ነሀሴ 18 ቀን 2015 አ.ም ሊያከብር ነው



**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት/ አዲስ ቻምበር/ የግሉን ዘርፍ በማጠናከር በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ የበኩሉን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የብሄራዊ ባንክ ቦርድ የውጭ ምንዛሬ ክፍፍል ማሻሻያ ላይ የወሰደው እርምጃ ለወጪ ንግድ ማደግ ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ተገለጸ




**በስታፍ ሪፖርተር**

በንግዱ ማህበረሰብ ዘንድ ከፍተኛ ቅራኔን ሲያስተናግድ የነበረው የውጭ ምንዛሬ ክፍፍል አዎንታዊ የፖሊሲ ምላሽ ማግኘቱ ንግድና ኢንቨስትመንትን ይበልጥ እንደሚያበረታታ ተስፋ ተደርጎበታል። የንግዱ ማህበረሰብ አባላት ከዚህ ቀደም በወጪ ንግድ ዙርያ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ክፍፍል ወይም ድርሻ በንግድና ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ዜጎችን የሚያበረታታ እንዳልነበር በዚህ ዙርያ ለአዲስ ቻምበር ሀሳባቸውን ሀሳባቸውን ገልጸዋል። ከዚህም ባለፈ የንግዱ ማህበረሰብ ንግድና ኢንቨስትመንትን እንዳያስፋፋ ብሎም ተጨማሪ የስራ እድል ለዜጎች እንዳይፈጥር የነበረው የውጭ ምንዛሬ ክፍፍል ቀመር አስቸጋሪ እንደነበር ገልጸዋል።

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

MIDROC INVESTMENT GROUP
Elfora Agro Industries P.L.C.
A Member of the MIDROC Investments Group Companies



ELFORA STANDS FOR NATURAL & QUALITY PRODUCTS !
Phone: +251-116-46-10-79, +251-116-45-03-61
Fax: +251-116-45-05-03
E-Mail: elforamarketing@gmail.com
mohzeki73@gmail.com
Website: midrocinvestmentgroup.com/en

# ርዕሰ አንቀጽ

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirma0357@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
እስራኤል ማንአየ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ዘካሪያስ አሰፋ-ሰብሳቢ
ሲሳይ ታደሰ- አባል
ካሳሁን ማሞ- አባል
አሸናፊ ምትኩ- አባል
ስዩም ጫኔ -አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ሐምሌ 2015 እትም

## ሰላም ለቢዝነስ፣ቢዝነስ ለሰላም!!!

በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በተለይም በኢትየጰያ የስራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበትና የምርት ማነስን የመሳሰሉ ችግሮች በስፋት ይስተዋላሉ፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ደግሞ አገር ለኢንቨስትመንት ምቹ እንድትሆን ማድረግና በሰላም ዙሪያ መስራት ይገባል፡፡

የኢንቨስትመንቱ ዘርፍ ምንም እንኳን ለሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ያለው አበርክቶ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ቢሆንም የተለያዩ ተግዳሮቶች አሉበት፡፡ በዋናነትም የሰላም እጦት፣የመስሪያ ቦታ ማጣት፣ ሙስና፣ የኃይል መቆራረጥና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ዘርፉን ከሚፈታተኑ ችግሮች መካከል ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚስተዋለው የሰላም ችግር በውጭም ሆነ በሀገር በቀል  ኢንቨስትመንቱ ላይ ፈታኝ እየሆነ መጥቷል፡፡ ችግሩም በረዘመ ቁጥር ኢንቨስትመንቱን እየጎዳው እንደሚሄድ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ሰላም ለኢንቨስትመንት ማደግና መስፋት የማይተካ ሚና አለው፡፡ በሀገራችን የተስተዋለው አለመረጋጋት በአንዳንድ ቦታዎች በኢንቨስትመንት ሥራው ላይ መስተጓጎል መፍጠሩ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ክስተት ወደፊትም ቢሆን የሀገሪቱን መልካም ገጽታ በማበላሸት ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የሚያሳጣ መሆኑን መረዳት ቀላል ነው፡፡

ኢንቨስትመንት በዋነኛነት በአንድ ሀገር ውስጥ ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር በመቀነስ የላቀ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በተለይም ወጣቱ፣ አዛውንቱ፣ ነጋዴው እንዲሁም ሰራተኛው ሰላሙን በማስጠበቅ የእድሉ ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ለዘርፉ መስፋፋት እያንዳንዱ ዜጋ የራሱን አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት፡፡

በማንኛውም መልኩ ኢንቨስትመንት ላይ የሚደርስ ጥፋት ደግሞ ዘርፉን መቀላቀል የሚፈልጉ ሌሎች ባለሀብቶችን ፍላጎት ይቀንሳል፡፡ ሰላም እና የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ የባለሀብቱ ፍሰት የበለጠ ስለሚጨምር በዚህ ጉዳይ ላይ ስራ መሰራት አለበት፡፡ አሁን በሰላም ላይ የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት፡፡ ሀገር  ያለ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማደግ ስለማይችል ሕብረተሰቡ ስለ ሰላም አስፈላጊነት መስበክ ይኖርበታል፡፡

ኢንቨስትመንት በባሕሪው የተረጋጋ ኢኮኖሚና ሰላምን ይፈልጋል፡፡ ሰላም በሌለበት ኢንቨስትመንትም ሆነ የስራ ዕድል መፍጠር አይቻልም፡፡ ሰላምና ኢንቨስትመንት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች በመሆናቸው ወጣቱ ኢኮኖሚ አመንጪ የሆኑ ተቋማትን በመንከባከብ የራሱንም ሆነ የሀገሩን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ በሰላም እጦት ምክንያት ከሚስተጓጎሉ ኢንቨስትመንቶች ጀርባ የበርካታ ዜጎች ጉሮሮ እንደሚዘጋ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዓመት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ለ3 ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በማቀድ በርካታ የሰው ኃይልን ይሸከምልኛል የተባለው የኢንቨስትመንቱን ዘርፍ ነው፡፡ ስለሆነም እያንዳንዱ ዜጋ ዘርፉን በመንከባከብ ተጠቃሚነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሰላማዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ሥርዓት ለንግዱ ዘርፍ ምቹ ሁኔታ ስለሆነ፣ በዚህ ምቹ ሁኔታ ውስጥ ዘርፉ ያሉበት ችግሮች ተስተካክለው ወደፊት ሊራመድ ይገባል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ በአንድ ጀንበር የማይሆን፤ ለውጥም በአንድ ጀንበር እውን ሊሆን እንደማይችል እሙን ነው፡፡

ለማጠቃለል ያክል የግሉ ዘርፍ ካለበት ችግር በማላቀቅ ኅብረተሰቡን ፍትሐዊ ተጠቃሚ የሚያደርግና በወጪ ንግድ ግኝት የአገራችንን ኢኮኖሚ የሚጠግን የንግድ ዘርፍ እንዲኖረን፣ የማይመለከተንና ድርሻ የሌለን ኢትዮጵያዊ የለንምና ሚናችን አንድ ጠብታም ብትሆን እሷኑ ሳንሰስት እንወጣ ፡፡

በነገራችን ላይ በኢትዮጵያ ጠንካራ የንግድ ትስስር መፍጠር ከተቻለ በየአካባቢው ሰላምና መረጋጋትን ለማስፈን ጉልህ ሚና እንደሚኖር አያጠራጥርም ፡፡ ጠንካራ የንግድና ኢኮኖሚ ትስስር መፍጠር በረጅም ጊዜ አስተማማኝ ሰላም ያመጣል፤ በዚህ ላይ ደግሞ ጠንክሮ መስራት ይገባል፡፡

ቀዳሚው የኢንቨስትመንት መደላድል ሰላም ነውና ሰላም በሌለበት፤ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ በተገታበት፣ ብቃት ያለው የሰው ሃይል በማይገኝበት፣ ሃብት በሚዘረፍበትና በማንኛውም አጋጣሚ ሊወድም በሚችልበት ሁኔታ ሃብት እርባን አይኖረውም፡፡ እናም ሰላም ከሌለ ኢንቨስትመንት አይኖርም፡፡ ሰላም ለቢዝነስ፣ቢዝነስ ለሰላም!!!!

TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458

## የብሄራዊ ባንክ ቦርድ የውጭ ምንዛሬ ክፍፍል ማሻሻያ...

ከ ገጽ 1 የዞረ

የውጭ ምንዛሬ ድርሻን አስመልክቶ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በተለያዩ ጊዜያት በዚህ ርእሰ ጉዳይ የውይይት መድረኮችን በማመቻቸት መንግስት ወይም ብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ ክፍፍልን እንዲያስተካከል የአድቮኬሲ ስራዎችን ሲያካሂድ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

እንደሚታወቀው በዚህ ጉዳይ አዲስ ቻምበር የቢዝነስ ማህበረሰቡን ለመደገፍ በመንግስት የሚወጡ መመሪያዎች የታለመላቸውን ግብ እንዲያሳኩ በማድረግ ለሀገሪቱ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚያበረከቱት አስተዋፆኦ እንዲጎለብት ከማድረግ አኳያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተቀማጭ የውጪ ምንዛሬ አካውንት እና አጠቃቀም መመሪያ “The Retention and Utilization of Export Earnings and Inward Remittances Directives No. FXD/79/2022” እንዲሻሻል ሰፊ ስራዎችን ሰርቷል፡፡

ይህ የቀድሞ መመሪያ በአባላቶቹ የንግድ እንቅስቃሴና አብዛኞቹ በውጪ ምንዛሬ እጥረት ሳቢያ የተፈጠሩ ችግሮችን የበለጠ የሚያባብስ እንደሆነ የንግዱ ማህበረሰብ አካላት አዲስ ቻምበር በተለያዩ ጊዜያት ባመቻቸው የውይይት መድረኮች ወቅት ሲያስረዱ ቆይተዋል፡፡ በተለይም መመሪያውን ተከትሎ በአምራች ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶች ከውጪ ለሚያስመጧቸው መለዋወጫዎች፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ እቃዎች፣ የኬሚካል እና መሰል ጥሬ ዕቃዎችን ለማግኘት እንዳላስቻላቸው አዲስ ቻምበር ለሚመለከታቸው በጥናት መልክ ሲያቀርብ እንደነበር ይታወሳል፡፡

በመሆኑም ከባንኮች ከሚያገኙት የውጪ ምንዛሬ 70% መቀነስ የማምረት ሥራቸውን ስለሚያስተጓጉል ምርታቸውን በተፈለገው መጠን እና ወቅት ለማምረት እንደሚቸገሩ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ም/ቤታችን በመገንዘብ እንዲስተካከል የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራ ሰርቷል፡፡

ስለሆነም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያወጣውን መመሪያ ከውጪ ምንዛሬ እጥረት ጋር ተያይዞ በኢኮኖሚውና በግሉ ዘርፍ ላይ የተከሰቱ ችግሮችን የበለጠ እንዳያባብስ መመሪያው በድጋሚ እንዲታይ እና እንዲሻሻል ንግድ ምክር ቤቱ በጥናት ላይ የተመሰረተ የአድቮኬሲ ስራ ሲሰራ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን አሁን የተደረገው አዲሱ የውጪ ምንዛሬ ክፍፍል ማሻሻያ ለግሉ ዘርፍ እድገት ትልቅ እርምጃ እና አስተዋጽኦም ይኖረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ብሄራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ ክፍፍሉ ቀደም ሲል ከነበረው 70/30 ወደ 50/50 እንዲስተካከል አድርጓል፡፡ 50% ለብሄራዊ ባንክ 40% የውጭ ምንዛሬውን ላመነጨው 10% ለባንኮች እንዲከፋፈል ተወስኗል፡፡

## አዲስ ቻምበር የአባላት ቀንን በመጪው ሀሙስ ነሀሴ 18 ቀን 2015 አ.ም ሊያከብር ነው

ከ ገጽ 1 የዞረ

አዲስ ቻምበር ከተመሰረተበት 1939 ዓ.ም ጀምሮ በንግዱ ህብረተሰብ ወይም በአባላቱ ድጋፍ ተቋማዊ ህልውናውን አስጠብቆ ላለፉት 76 ዓመታት የተጓዘ ሀገራዊ ተቋም ነው፡፡

ንግድ ምክር ቤቱ የንግዱ ማኅበረሰብ መሰባሰቢያ ጥላ ሆኖ ለዘመናት በማገልገል አባላቶቹ የሀገሪቱ ምጣኔ ሀብት የጀርባ አጥንቶች፣ የእድገት ምሶሶዎች ሆነው በጋራ ሰርተውና ተባብረው አሁን ለደረሰበት ደረጃ አድርሰውታል፡፡

በመሆኑም ንግድ ምክር ቤቱ ጠንካራ የግል ዘርፍ እንዲፈጠር አባላቱና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት ፣ በጋራ ተገናኝተው የሚመክሩበት እና የሚበረታቱበት አመታዊ የአባላት ቀን ሀሙስ ነሃሴ 18፣2015 አ.ም በስካይ ላይት ሆቴል እንደሚካሄድ ተገልጿል፡፡


በእለቱ በርካታ የኩባንያ ሃላፊዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ የመንግስት ተቋማት እና የማህበራት ተወካዮች፣ ምሁራን እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ይገኛሉ፡፡

## የዓለም አቀፍ የጭነት አስተላላፊዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን /ፊያታ/ ጉባዔ በአዲስ አበባ መካሄዱ ኢትዮጵያ በዘርፉ ጥሩ እመርታ ለማሳየቷ አመላካች መሆኑን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ(ዶ/ር) ገለጹ

ለሁለት ቀናት የተካሄደው የዓለም አቀፍ የጭነት አስተላላፊዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን /ፊያታ/ ጉባዔ በአዲስ አበባ ተካሄዷል፡፡

በጉባዔው መክፈቻ ላይ የተገኙት የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ(ዶ/ር) ይህ ጉባዔ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ መካሄዱን ገልፀዋል፡፡ የጭነት ማስተላለፉ ለአገር ኢኮኖሚ ግብዓትና ሸቀጦችን ወደ ገበያ ለማቅረብም ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

ከውይይቱም በጭነት ምልልሱ የሚታዩትን ችግሮች በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ማመላከትን ዓላማ ያደረገ ነው ብለዋል፡፡



ዓለም አቀፍ የጭነት አስተላላፊዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን 100ኛ ዓመት በዓልን እ.ኤ.አ በ2026 በኢትዮጵያ እንዲያዘጋጅ ጥያቄ መቅረቡንም ጠቁመዋል፡፡ የፌዴሬሽኑ ዋና ዳይሬክተር ጄነራል ስቴፈን ግራበር(ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በሎጂስቲክስ ዘርፍ ባለፉት ዓመታት ጠንካራ የሚባሉ ሥራዎችን መሥራቷን ገልፀዋል፡፡

ኢትዮጵያ በ2026 የዓለም የእቃ አስተላላፊዎች ማኅበራት ፌዴሬሽን የ100ኛ ዓመት በዓልን ለማዘጋጀት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ ከማድረግ አንፃርም የዚህ ጉባዔ መካሄድ ሰፊ እገዛ እንደሚኖረውም አንስተዋል፡፡

ከሦስት ዓመት በኋላ ለሚካሄደው 100ኛ ዓመት ጉባዔ የዓለም አገራት የሎጂስቲክስ ማኅበራት ኃላፊዎችን ጨምሮ ከ2 ሺህ 500 በላይ እንግዶች እንደሚሳተፉ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ለኢትዮጵያ ትልቅ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል፡፡

# አዲስ ቻምበር ከአዳማ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ጋር በጋራ መስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ



በከፍያለው ዋሲሁን

ስምምነቱን የሁለቱ ንግድ ምክር ቤት ዋና ፀሀፊዎች በአዲስ ቻምበር የቦርድ መስብሰቢያ ሃምሌ 27 ቀን 2015 ዓ.ም ተፈራርመዋል ፡፡ የአዲስ ቻምበር ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ቤተ ማርያም ስምምነቱ በንግድ ምክር ቤቶች ብቻ ሳይታጠር የሁለቱ ከተሞች ስምምነት አድርገን ልናየው ይገባል ብለዋል ፡፡ አክለውም በንግድ ስራና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ላይ ያሉ ስራዎችን በጋራ ለመስራት መዘጋጀት ከሁለቱ ንግድ ምክር ቤቶች የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ የንግድ ምክር ቤቶች በቅንጅት መስራት ላይ ውስንነት እንዳለባቸው የጠቀሱት አቶ ሺበሺ ፣የግል ዘርፍ አጋርነትን ለመፍጠር ምክር ቤታቸው እየሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል ፡፡ በኬኒያ የግሉ ዘርፍ ህብረት እንዳለ ጠቅሰው በኢትዮጵያም ሁሉንም ንግድ ምክር ቤቶች አቅፎ የሚያንቀሳቅስ መሰል የግሉ ዘርፍ ጥምረት አስፈላጊ መሆኑን አስምረውበታል ፡፡

ይህ ስምምነት ከዚህ አንጻር የላቀ ጠቀሜታ እንደሚኖረው እምነታቸውን ገልፀዋል ፡፡ ከአዳማ ንግድ ምክር ቤት ጋር ስምምነት ስናደርግ የመጀመሪያችን አይደለም ያሉት አቶ ሺበሺ አስራ ስምንት የመግባቢያ ሰነዶችን ከሌሎች ንግድ ምክር ቤቶችና ከመንግስት ተቋማት ጋር መፈራረማቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የአዳማ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ዋና ፀሀፊ አቶ ሃጂ ከተማ በበኩላቸው ምክር ቤታቸው ከአዲስ ቻምበር ጋር ለመስራት የወሰነው ጠንካራ ንግድ ምክር ቤት በመሆኑና ብዙ የሚማሩበት ንግድ ምክር ቤት በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ንግድ ምክር ቤቶች የተፈራረሙት ስምምነት በምርምርና የአድቮኬሲ ስራዎችን ፣ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ፣ በንግድ ትርዒት ዘርፎች ላይ በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸው ነው ሲሉም ጠቅሰዋል፡፡ ንቁና የበቃ ነጋዴ ለመፍጠር የሚያግዙ ስልጠናዎች ከመስጠት ባሻገር የተለያዩ የውይይት መድረኮችን ምክር ቤታቸው እየሰራ መሆኑን አቶ ሃጂ ተናግረዋል፡፡

ይሁንና አዲስ ቻምበር የተደራጀ አቅምና ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እንዳሉት ጠቅሰው በጋራ መስራታቸው ንግድ ምክር ቤታቸውን ተጠቃሚ ያደርገዋል ብለዋል ፡፡

አዲስ ቻምበር ትልልቅ ስራዎችን እየሰራ የሚገኝ አንጋፋ ንግድ ምክር ቤት መሆኑን ያነሱት ደግሞ የኦሮሚያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ቦርድ ፕሬዝዳንትና የአዳማ ንግድ ምክር ቤት የቦርድ አባል አቶ አበበ በንቲ ናቸው ፡፡ ከአዲስ ቻምበር ትልቅ ትምህርት ማግኘታቸውንና በቀጣይም በመደጋገፍ በመስራት ለውጥ ለማምጣት ስምምነቱ ትልቅ እገዛ እንደሚኖረው ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡

# በሃገራዊ ምክክሩ የግሉ ዘርፍ በንግድ ምክር ቤቶች በኩል መወከል እንዳለበት ተገለጸ




የአዲስ አበባ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ከኢኒሽየቲብ አፍሪካ ጋር በመተባበር በመጭው ሃገራዊ ምክክር ላይ የግሉ ዘርፍ ሚናን አስመልክቶ የውይይት መድረክ አካሂዷል፡፡ የግሉ ዘርፍ በሃገራዊ ምክክሩ ዋና ተዋናይ መሆን እንዳለበት አጽንኦት በተሰጠበት የውይይት መድረክ ላይ ከብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነር መላኩ ወልደማርያም ኮሚሽኑ ቅድመ ዝግጅቱን በመጨረስ ወደ ትግበራ ለመግባት ተሳታፊዎችን የመለየት ስራ እየሰራ መሆኑን አንስተዋል፡፡

የተሳታፊዎች ልየታ ተጠናቆ ሲያልቅ አጀንዳዎች ለኮሚሽኑ እንደሚልኩም ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የግሉ ዘርፍ ያለውን የገንዘብ የእውቀት እና የቁሳቁስ አቅም ድጋፍ እንደሚያደርግ እምነታቸው እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ የኮሚሽኑ የመጀመርያው መርህ አካታችነት መሆኑን ተከትሎ ይህን ማሳካት እንዲቻል መሰል ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተጠቁሟል፡፡ በመድረኩ ለውይይት መነሻ የሚሆን ልምዳቸውን ካካፈሉት መካከል በውጭ ግንኙነት ስራዎች ልምድ ያላቸው አብደታ ድሪብሳ( ዶ/ር) አንዱ ሲሆኑ ከሌሎች ሃገሮች ተሞክሮ በመነሳት ኮሚሽኑ ሁሉን ለማስታረቅ የሚሆን ማእቀፍ ያለው እና እምነት የሚጣልበት መሆን እንዳለበት ጠቅሰዋል፡፡ ከዚህም አንጻር አካታችነት እና ቁርጠኝነት አለመኖር ምክክሩ ካልተሳካባቸው ሀገሮች የተገኙ ልምዶች መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋም ዳይሬክተር አቶ ዮሃንስ ወ/ገብርኤል ንግድ መንቀሳቀስን ፍትህን የሚፈልግ እንደመሆኑ የምክክሩ አስፈላጊነት ወሳኝ መሆኑን አንስተው የንግዱ ማህበረሰብ በምን መልኩ ይወከል የሚለው ትኩረት የሚፈልግ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

መንግስት በሀገራዊ ምክክሩ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ እና በልኩ አስተዋጽኦ እንዲያበርክት ከተፈለገ በአዋጅ የተቋቋሙ የንግድ ምክር ቤቶችን በዋናነት ማሳተፍ እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ ይህ ካልሆነ ስኬታማ ምክክር ለማድረግ እንቅፋት እንደሚሆን ጠቁመዋል፡፡

# በክልሎች ይሰጥ የነበረው የአስመጪና ላኪዎች የንግድ አገልግሎት ከሐምሌ 1/2015 ዓ.ም ጀምሮ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ብቻ እንዲሰጥ ተወሰነ

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ዛሬ ሀምሌ 3 ቀን ይፋ ባደረገው መረጃ በክልሎች ይሰጥ የነበረው የአስመጪዎችና ላኪዎች ንግድ አገልግሎት ከሐምሌ 1/2015 ዓ.ም ጀምሮ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በኩል አገልግሎቱ እየተሰጠ ይገኛል ብሏል፡፡

የኦንላይን ንግድ ምዝገባና ፈቃድ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በክልሎችና በሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች በኩል ይሰጥ የነበረው የአስመጪና ላኪ የንግድ አገልግሎት አስተዳዳራዊ ክፍተቶች የታዩበት፣ የኮንትሮባንድ ንግድ የተበራከተበት በመሆኑና በወቅቱ አገልግሎቱ ያልወረደላቸው ክልሎች የመልካም አስተዳደር ጥያቄ በማንሳታቸው ሚኒስትር መስራ ቤቱ ይህን ችግር ለመፍታት የአስመጪና ላኪዎች ንግድ አገልግሎት ከሃምሌ 1/2015 ዓ.ም ጀምሮ በፌዴራል ተግባራዊ እንዲሆን መወሰኑን ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ አስታውቋል፡፡ የኦንላይን ንግድ ምዝገባና ፍቃድ አገልግሎት ከሃምሌ 1/2013 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ መደረጉን ተከትሎ ማንኛውም አስመጪና ላኪ ነጋዴ የትም ማሄድ ሳይጠበቅበት ሲስተሙን በመጠቀም ባለበት ቦታ ሆኖ አገልግሎት ማግኘት ይችላል ሲል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስታውቋል፡፡

# ጎስቋላ ጋራዦቻችን እስከመቼ ...?



**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

አገራችን በየጊዜው በነገሱ ብልህ እና አርቆ አሳቢ መሪዎቿ አማካኝነት የአውሮጳን ሰልጣኔ ትሩፋት ከአውሮጳውያኑ ወዲያው ወስደው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ወደ አገራቸው በማስገባት በዘመናቸው የሚቀድማቸው ያለ አይመስልም ነበር፡፡ በተለይ ከአጼ ቴዎድሮስ የጀመረው የአውሮጳን ቴክኖሎጂ ማምጣት እና ለሕዝብ ጥቅም ላይ ማዋል እስከ ድሕረ የጣልያን ወረራ የቀጠለ ነበር፡፡

ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ስንል በዘመኑ የሰለጠነው ዓለም ከምንለው ይከወኑ ከነበሩት ቴክኖሎጂዎች መካከል እንደ ልዩ ልዩ የጦር መሳሪያዎች፤ባቡር፤ ስልክ ፤ቧንቧ ውሃ፤መኪና፤ ፖስታ አገልግሎት፤ጋዜጣ ወዘተ.... ለጊዜው እነዚህ ይብቁን፡፡ ከእነዚህ አንዱን ብቻ አንስተን ብናወራ ከሁሉም የአፍሪቃና ከብዙ የዓለም አገራት ሕይወት ታሪክ በላይ ነው፡

ለዛሬው የመኪና ነገር እናንሳ፡ ፡ አገራችን የመኪና ወይም የአውቶሞቢል ታሪክ ቢያንስ ከ130 አመት በላይ ነው ይባላል፡፡ የመጀመሪያው አሽከርካሪ በወቅቱ የነበሩት ንጉሠ ነገሥቱ አጼ ምኒልክ ነበሩ ሲል ታሪክ ይነግረናል፡፡

በእነዚያ ወራት ወደ አገራችን በገባችው ኦቶሞቢል ሳቢያ ሰንበት ብሎ ስለተጀመረው የተሽከርካሪ ጠጋኞች በውጪ አገር ሰዎች እንደተከፈቱ ይነገራል፡፡ የእነዚህ ጋራዦች መከፈት ለአገሬው ልጆች ዋና የቴክኖሎጂ እና የመካኒክ ጥበብ መሸጋገሪያ ቦታዎች ሆነው ለብዙ አመታት ቆይተዋል፡፡

የመኪና ቴክኖሎጂ መምጣት ተከትሎ በኦቶሞቲብ ዘርፉ ከተወለዱ የቢዝነስ ዓዞች መካከል የመለዋወጫ፤ቅባት እና ዘይቶች፤የጎማ፤የመስተዋል፤ የ መ ን ገ ድ ፤ የ ት ራ ፊ ክ ፖሊስ፤ የአሽከርካሪ ማሰልጠኛዎች፤አንዲሁም ጥገና የሚሰጡ ጋራዦች ይገኛሉ፡

በከተማችን ብቻ የሚንቀሳቀሱትን ጋራዦች ብቻ ብንመለከት ምን ያህሉ በጥራት፤በደረጃ እና በሥራ ቦታ ተስማሚነት ቢመዘኑ ”ጋራዥ” የሚለው ሥም ይገባቸው አንደሆነ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች መልስ ቢሰጡበት ይሻላል፡፡

አንዲት ፍሬ መኪና አካልም ይሁን አንዲት ንዑስ መለዋወጫ በማይመረትበት አገር እነዚህ በየቀኑ የሚርመሰመሱት መኪናዎች እስትንፋስ የሚሰጡት እዚሁ በየመንገዱ፤በየጥጋጥጉ የተወሸቁት ጋራዦቻችን ናቸው፡፡ በከተማችን ወደ 100 ሺህ የሚጠጉ ሰዎች የኑሮ ህልውና ከነዚህ ጋራዦች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚተሳሰር ነው፡፡

በከተማችን የሚገኙ ባለጋራዦች ወደ አንዳንዶቹ ጠጋ ብለን ብናወጋ ጋራዦች በውስብስብ ችግሮች ውስጥ እንደሚገኙ ይናገራሉ፡፡ ዋናው መንግሥት ለጋራዥ ዘርፉ የሰጠው ትኩረት አናሳ ነው ሲሉ ይጀምራሉ፡፡



### “ጋራዦች በማስተር ፕላን ቢካለሉ አብዛኛው ችግሮቻችን ይፈታሉ”

አቶ ዝናቡ መንገሻ ከአዲስ አበባ የአውቶሞቲቭ ማሕበር የቴክኒክ ኮሚቴ ገለጻ ጋራዦች ብዙ አይነት ችግሮች አሉባቸው፡፡ ብዙ ጋራዦች ስራቸውን የሚሰሩት በትናንሽ የግለሰቦች ግቢ ውስጥ ነው፤ ለአደጋ የተጋለጡ ናቸው፡፡

ከአንድ ጋራዥ ቀጥሎ የመኖሪያ ቤት ወይም ሆቴል ወይም ክሊኒክ ሊኖር ይችላል፡፡ አብዛኞቹ በመኖሪያ ቤቶች ተከብበው ነው የሚሰሩት ይላሉ፡፡ እኛም በአዲስ አበባ ከተማ በተለይ በቄራ አካባቢ የታዘብነው ይህን ሀቅ ነው፡፡

አብዛኞቹ ለሰራተኞች ጤና እና ለሥራ ምቹ አይደሉም፡፡ የቆሻሻ ማስወገጃ ብሎ ነገር በጋራዦች መንደር የሚታሰብ አይደለም፡፡ የኤሌክትሪክ እና የተቀጣጣይ ነገሮች ጥንቃቄ ሥርዓት የላቸውም፤ ክፉን ያርቅላቸውና ድንገተኛ የእሳት አደጋ ቢነሳ የማጥፊያ መኪናዎች የሚደርሱበት መግቢያ መንገድ የሌላቸው ናቸው፡፡

የአዲስ አበባ ኦቶሞቲቭ ማሕበር በኦቶሞተቭ ዘርፍ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ብዙ ርቀት እንደተጓዘ አስታውሰው ከተለያየ የከተማዋ የቢሮ ኃላፊዎች ጋር ተደጋጋሚ ውይቶች መደረጋቸውን ይናገራሉ፡፡ ጋራዦች አንደ ክሊኒኮች፤ሆቴሎች፤ኮንስትራክሽን ኩባንያዎች ወጥ የሆነ ደረጃ እና የአሰራር ሥርዓት አንዲበጅላቸው ጠይቀዋል፡፡

በተለይ የጋራዦች ነገር በአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላን ውስጥ ያልተካተተ በመሆነ አንዱ ችግር በየጥጋጥጉ ትናንሽ የጥገና ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ አንዳንዶቹም በአውራ መንገዶች ዳር ጥገና አገልግሎት ሲሰጡ ይታያል፡፡ ስለዚህ የከተማዋ አስተዳደር ትኩረት ሰጥቶ የጋራዦች ጉዳይ መልክ አንዲይዝ ማድረግ እንዳለበት አሳስበዋል፡ ፡ ስለዚህ በተመረጡ የከተማዋ ቦታዎች ላይ የኦቶሞቲቭ መንደሮች መመስረት አለባቸው ይኸውም ከላይ ለተነሱት የዘርፉ ችግሮች በአብዛኛው የሚመልስ ይሆናል ይላሉ፡፡



ዛሬ በኮምፒዩተር ታግዘው ምርመራ እና ጥገና የሚደረግላቸው እና በርቀት መቆጣጠሪያ የሚታዘዙ ዘመናዊ ተሽከርካሪዎች ወደ አገራችን በገፍ እየገቡ ነው፡፡ ስለዚህ በዚህች ዓለማቀፍ ከተማ የሚገኙ ጋራዦችም በዚያው ልክ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ ሚሟላት ይገባናል፡፡ በከተማዋ ማስተር ፕላን የኦቶሞቲቭ ዞን ከተመለከትን የመለዋወጫ ፤የቅባት፤የጎማ ወዘተ አቅራቢዎች በዚያው ዙሪያ ይኖራሉ፡፡

### “በከተማዋ ያሉ ጋራዦች ለአንደ ቀን ሥራ ብናቆም የኛ ችግር ምን ያህል ጎልቶ እንደሚወጣ እና ጋራዦች በየቀኑ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ድርሻ በጣም ጉልህ ሆኖ እንደሚወጣ ይሰማኛል።”

የቤዛ ኦቶሞቲቭ ጋራዥ ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮናስ ኃይሉ የጋራዥ ሥራ በጣም ሰፊ ነው ይላሉ፡ ፡ በከተማ ብቻ ብናይ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ወጣቶች በክረምት የዕረፍት ጊዜያቸውን ዕውቀት እየገበዩ የሚያሳልፉት ከእኛ ጋር ነው፡፡ ብዙዎች ዛሬ አንቱ የሚባሉ መካኒኮች ለመሆን የበቁት በእኛ አማካኝነት ነው፡፡ ዛሬም ድረስ በየአመቱ ከኮሌጆች የተመረቁ ከእኛ ዘንድ ልምምድ እያደረጉ ናቸው፡፡ የአውቶሞቲቭ ዘርፍ ጥቅሙ በጣም ሰፊ ነው፡፡ እኔ ሳስበው ይላሉ አቶ ዮናስ “ በከተማዋ ያሉ ጋራዦች ለአንድ ቀን ሥራ ብናቆም የኛ ችግር ምን ያህል ጎልቶ እንደሚወጣ እና ጋራዦች በየቀኑ በኢኮኖሚው ላይ ያላቸው ድርሻ በጣም ጉልህ ሆኖ እንደሚወጣ ይሰማኛል፡፡”

የኦቶሞቲቭ ዘርፉ በቴክኖሎጂ ሽግግር፤ አንዳንድ ውድ መለዋወጫዎችን አዛምዶ (ሞደፊክ) የማበጀት ክህሎቶችን፤ ከሁሉ በላይ ተሽከርካሪዎች ዕድሜ የሚያራዝሙት እና የውጪ ምንዛሬ የሚያድኑበት ቦታዎች ናቸው፡፡

የኦቶሞቲቭ ዘርፉ በባሕሪው የማይገባበት የሥራ ዘርፍ የለም ፡ ፡ ከድሮ ጀምሮ ጋራዦች እንደው በተገኘው ቦታ በትንንሽ ገንዘብ ነው የሚጀመሩት፡፡ በከተማችን የሚርመሰመሱት ከባድ መኪኖች፤ አውቶብሶች እና ትናንሽ ተሽከርካሪዎች አዲሶቹም ይሁን አድሜ የጠገቡት እስከዛሬ ድረስ ሕይወታቸው የቀጠለው፡፡

ለመሆኑ መኪና ወደ አገራችን መግባት ከጀመረበት አንስቶ እስከዚህ አመት የተመረቱ አዳዲስ እና እጅግ የዘመኑ መኪናዎች በሚገቡት ልክ አብሮ የሚሄዱ ደረጃቸው እና በማስተር ፕላን የተካለሉ ጋራዦች አንዲኖሩን ያስፈልጋል ፡፡

እዚህ ላይ ከተማችን በፈጣን ዘመናዊ የመሠረተ ልማቶች ዕድገት የሚታይባት እና የዓለማቀፍ የስበት ማዕከል እንደሆነች ባለችበት በአሁኑ ወቅት ከተማችንን የሚመጥኑ ፤ ደረጃውን የጠበቀ የኦቶሞቲቭ ዘርፍ ፤አድራሻቸውም በማስተር ፕላን የተደገፈ እና ከተማዋን ያማከለ ቢሆን የኦቶሞቲቭ መዳረሻ መንደሮች እውን ቢሆኑ አንዱ የዘርፉን ችግር የሚፈታ ይሆናል ሲሉ የኦቶሞቲቭ የዘርፍ ማሕበራት አባላት ምክረሃሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ የትራንፖርት ቢሮ፤ የከተማችን ማስተር ፕላን መ/ቤት እና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ይህንን ዘመን ያስቆጠረ ችግር መፍትሔ ያበጁለታል የሚል ተስፋ አለ፡፡ ሰላም!!

# "ቆሻሻ አንሺ እንፈልጋለን" የምትል የጨረታ ማስታወቂያ አየሁ...

- **የሠራተኛ መነሻ ደመወዝ እርከን መንግሥት በአስቸኳይ እንዲያወጣልን እንፈልጋለን አቶ አክሊሉ አወቀ ፤ የሸበሌ ጽዳት አገልግሎት ኩባንያ ሥ/አስኪያጅ**



የዘመናዊ አኗኗር ዘይቤ እና ከተሜነት መስፋፋት ተከትሉ አዳዲስ የአገልግሎት ዘርፎች ብቅ ብቅ ማለት ከጀመሩ ሰንብተዋል። ከእነዚህም መካከል ልዩ ልዩ የመንጓጓ አገልግሎት ፤የጥበቃ፤በኮንስትራክሽን ውስጥ በፍሳሽ ማስወገድ ፤ የሕንጻ አካላት ተከላ፤ በማሽነሪዎች አቅርቦት እያለ እስከ በሰሉ ምግቦች የሚያቀርቡ ድርጅቶች ይገኙበታል። በተለይ በአዲስ አበባ እና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች አሁን ላይ በብዛት የሚታዩት የጽዳት አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ናቸው። በዚህ ዘርፍ ከተሰማሩት ሥራ ፈጣሪዎች አንዱ የዛሬው አንግዳችን አቶ አክሊሉ አወቀ ይባላሉ። ትውልዳቸው እና እድገታቸው በቀድሞው በባሌ ክክሀገር ሲሆን ፤የኮሌጅ ትምህርታቸውን በአ.አ ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው በሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሙያ ተመርቀዋል። በተለያዩ የመንግሥት እና የግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው አገልግለዋል። ዛሬ ላይ የሸበሌ ጽዳት ኩባንያ ባለቤት እና ሥራ አሥኪያጅ ናቸው። ከአንግዳችን ጋር ስለአነሳሳቸው ፤የጽዳት አገልግሎት ሲጪ ዘርፍ፤ዕድሎች እና የፖሊሲ ተግዳሮቶችቶች ዙሪያ ከባልደረባችን ይድነቃቸው ዓለማየሁ ጋር ቆይታ አድርገዋል።

**ንግድና ልማት:** ስለ አጠቃላይ የጽዳት ቢዝነስ ዘርፍ እናንሳ?

**አቶ አክሊሉ:** የጽዳት ቢዝነስ በአገራችን በቅርብ ጊዜ የተጀመረ ሥራ ነው ማለት ይቻላል። በነገራችን ላይ በውጪው ዓለም በጣም የተለመደ እና የታወቀ ሙያ ነው። ሥራውም በሥልጠና እና የሙያ ብቃት የሚጠይቅ ፤ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ ወጣቶች ተቀጥረው የሚተዳደሩበት የሥራ ዘርፍ ነው። ለምሳሌ በሰሜን አሜሪካ ብቻ እስከ 3 ሚሊዮን የሚጠጉ ዘጎች እንጀራቸው ይኸው የጽዳት ዘርፍ ነው። ወደ እኛ አገር ስንመለስ በዚህ ዘርፍ የተሰማራነው ቁጥራችን እና የአገልግሎት አድማሳችን ገና ነው፡ አብዛኛው ሕ/ሰብ ዘንድ ስለኛ ያለው መረጃ ገና ነው።

**ንግድና ልማት:** በዘርፉ ያላችሁ አንቀሳቃሾች ቁጥራችሁ ምን ያህል ነው?

**አቶ አክሊሉ:** በአዲስ አበባ ውስጥ ብቻ ወደ 20 እንሆናለን።

**ንግድና ልማት:** ለመሆኑ እርስዎ ወደ ጽዳት ቢዝነስ የገቡበትን ሁኔታ ቢነግሩን?

**አቶ አክሊሉ:** በአንድ ወቅት በግሌ በትርፍ የሂሳብ ስራ እሰራ ነበር። ታዲያ አንድ ቀን ከትርፍ ጊዜ ሥራ ወደ ቤት ስመለስ አንድ ጋዜጣ ላይ ተመለከትሁ። ቆሻሻ የሚያነሳ ድርጅት አለ ማለት ነው ? ስል እራሴን ጠየቅሁ። ስለዚህ ቢኖር ነው ማስታወቂያ ማውጣታቸው አልኩኝ እና መረጃ ማሰባሰብ ጀመርኩኝ። እውነትም በጽዳት አገልግሎት ዘርፍ ገና ያልተነካ ዘርፍ ነው። በኋላ በዚህ ዘርፍ ለመሰማራት የንግድ ፈቃድ ስለሚጠይቅ ፈቃድ አወጣሁኝ። የዚያ ጨረታ ጊዜው ባለማለቁ እኔም በያዝኩት አዲስ የንግድ ፈቃድ ተወዳደርኩኝ። ያኔ ለሥራው አዲስ ስለነበርኩኝ ጨረታውን አላሸነፍኩም። ቢያንስ 20 እና 30 ጊዜ በኋላ ነው ጨረታ ማሸነፍ የጀመርኩት። ከዚያ በኋላ ሥራየን ለቅቄ የሙሉ ጊዜዬን እና ትኩረቴን በዚህ ሥራ አድርጌ አዲሱን የግል ሥራየን ለመጀመር ወሰንኩኝ።

**ንግድና ልማት:** የጨረታ ነገር መቼም ሁሌም አስቸጋሪ ነው?

**አቶ አክሊሉ:** አዎን ጨረታ ማለት በጣም ለሙስና እና ለአድሎአዊ አሠራር የተመቸ ነው። ጨረታ ሲባል ሁሌም በጥቅም ትስስር የሚካሄድ ነው። ነገር ግን ቁጥራቸው ባይበዛ ነው እንጂ ንጹሕ እና ግልጽ የጨረታ ባሕል ያላቸው መ/ቤቶች አሉ። በእኔ ግምት ለእኛ ፤ለአገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች ትልቁ ፈተና አገልግሎት ፈላጊ ድርጅቶች በኩል የሚካሄድ የጨረታ ሥርዓት ። ውል ሰጪ ድርጅቶች የጨረታ አሰራራቸው በሙስና እና በጥቅም የተሳሰረ፤ግልጽነት የጎደለው እንደሆነ በሰፊው ይታያል።

**ንግድና ልማት:** ደንበኞቻችሁ እነማን ናቸው ?

**አቶ አክሊሉ:** የእኛ ደንበኞች አብዛኞቹ የንግሥት መ/ቤቶች ናቸው። የሚኒስቴር መ/ቤቶች፤ዩኒቨርሲቲዎች፤ትላልቅ ሕንጻዎች፤ሆቴሎች የመኖሪያ አፓርትመንቶችም ፋብሪካዎች፤ ሆስፒታሎች፤የስብሰባ አዳራሾች ይገኙበታል።

**ንግድና ልማት:** መንግሥት በቅርቡ ኤክትሮኒክ ጨረታ እንደጀመረ ይነገራል።

**አቶ አክሊሉ:** አዎን በመንግሥት በኩል የቨርቹዋል ፕሮኪዩርመንት መጥቷል። በዚህ የቨርቹዋል ጨረታ ላይ ተሳታፊዎች ነን። የሸበሌ የጽዳት ኩባንያ ሠራተኞች የግዢ ኤጀንሲ የሚሰጠውን ስልጠና ወስደናል። በቨርቿል ጨረታ አካሄድ ጨረታዎችን የማሸነፍ ዕድላችን ጨምሯል። ስለዚህ መንግሥት ይህንን በማድረጉ እኛ በጣም ደስተኞች ነን።

**ንግድና ልማት:** ረገኘርም ሕንጻዎችን ማጽዳት እና ኬሚካሎችን መጠቀም በሠራተኞች ጤና ላይ አደጋ አለው ?

**አቶ አክሊሉ:** አውነት ነው ። እኛ ለሰራተኞቻችን በመጀመሪያ ሥልጠና እና ደህንነት አጠባበቅ ዘዴዎችን ትምህርቶችን እናስተምራለን። በዚያም አስፈላጊ የሰራተኞች የደህንነት አልባሳት እና ቁሳቁስ በውድ ዋጋም ቢሆን ገዝተን እና ቀርባለን። ይሄ ለሥራ ተብሎ ብቻ ሳይሆን ለዜጎቻችን የምናደርገው ግዴታችን ነው ብለን ስለምናምን ነው። ለዚህም ነው መንግሥት ውድ የሆኑ አስፈላጊ የጽዳት ማሽነሪዎች የጤና መከላከያ አልባሳት እና ተዛማጅ ቁሳቁስ ከቀረጥ ነጻ አድርጎልን ለተወሰነ ጊዜ እንዲደግፈን የምንጠይቀው።

**ንግድና ልማት:** በጽዳት አገልግሎት ዘርፍ የፖሊሲ ተግዳሮቶች ካሉ

**አቶ አክሊሉ:** ለምሳሌ አዲስ አበባን እንውሰድ ። ከተማይቱ በጣም በፍጥነት ወደ ዘመናዊ የግንባታ እና መሠረተ ልማት ሽግግር ላይ ትገኛለች። እዚህ ላይ የመንግሥት እይታ በጣሙን ያስፈልጋል። ይህም ማለት በርካታ አዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎች ወደ ዘርፉ እንዲገቡ መንግሥት የተለያየ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን በተለይ ሰማይ ጠቀስ ለሆኑ ለረጃጅም ሕንጻዎች ጽዳት የሚውሉ ዘመናዊ ማሽኖች ወደ አገር ውስጥ ማስበገባት እንዲችሉ ከታክስ እና ከቀረጥ ነጻ ድጋፍ ማድረግ አለበት እላለሁ። ከዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ከውጪ የሚገቡ ኬሚካሎች በአገር ውስጥ እንዲተኩ ኬሚካል አምራቾችንማበረታታትያስፈልጋል። ምክንያቱም የጽዳት ሥራ ሁሌም የሚሰራ እና አቅርቦቱ ተቀጥያ እና አስተማማኝ መሆን አለበት። ስለዚህ አሁን ያለውን የከተሞች መስፋፋት አዝማሚያ ስንቃኝ፤ በተለይ አዲስ አበባን እንደስሟ አዲስ እና ንጹህ፤ ደረጃዋን የጠበቀች የአፍሪቃ መዲና እንድትሆን እኛን መንግሥት መደገፍ እና ለጥያቄዎቻችን ትኩረት ሰጥቶ መመለስ አለበት። በቃ በአጠቃላይ እንደኛው አንግዲህ የሠራተኞች የመነሻ የደሞዝ ስኬል አዋጅ የደሞዝ ቦርድ ተቋቁሞ የመነሻ ደሞዝ እርክን እንዲወጣ መንግሥት ቢደግፈን፡2ኛ የጽዳት ዕቃዎች ከቀረጥ ነጻ ተደርጎልን ማስገባት ብንችል፤ የሥልጠና እና የምክር ድጋፍ መንግሥት ለጽዳት ሴክተሩ ቢያደርግ ከፍተኛ የሥራ ዕድል የምንፈጥርበት ሴክተር ነው የሚሆነው።

**ንግድና ልማት:** ያኔ ተቀጥረው በሚሰሩ ጊዜ ደመወዝ እንዴት ነበር?

**አቶ አክሊሉ:** አይ ... ያኔ በወር 3 ሺህ ብር አካባቢ ነበር። ያኔም ለእኔ እና ለቤተሰቦቼ አይበቃም ነበር። ያኔም ትርፍ ሥራዎችን በግሌ እየሰራሁ እራሴን በራሴ እደጉም ነበር።

**ንግድና ልማት:** ማሕበር አላችሁ ?

**አቶ አክሊሉ:** በምሥረታ ላይ ነን በቅርቡ በማሕበራችን በኩል የጋራ ድምጻችንን እናሰማለን ፤አዲስ ቻምበርም አንዲያግዘን አንፈልጋለን።

**ንግድና ልማት:** የአገልግሎት ሥራ ላይ አለመገባባቶች እና ውዝግቦች ይስታዋላሉ ?

**አቶ አክሊሉ:** አንደ ማንኛውም ሻጭ እና ገዥ በንግድ ግንኙነት ውስጥ አለመግባባቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ሁሉ ፤ በአገልግሎት ዘርፍ ላይ አንዲሁ ከደንበኞች በኩል የሚነሱ ቅሬታዎች አሉ። የጽዳት አግልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ማሕበራችን በኩል ወጥ የሆነ ፤ በሁሉም አባላቱ ዘንድ ግልጽና ተጠያቂነት የተላበሰ የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ አንደርጋለን። ይህም ከፍላጎት በኩል ለሚነሱት እንደ አገልግሎት ጥራት መጓደል፤ ሥራን በተያዘለት ጊዜ አለማጠናቀቅ ወዘተ ችግሮችን ከዘርፉ ለማስወገድ ይበጃል።

**ንግድና ልማት:** ይሄ ቀረ የሚሉት ካለ ?

**አቶ አክሊሉ:** በዚህ አጋጣሚ የንግዱ ሕብረተሰብ በተለይ አገልግሎቱን የሚፈልጉ የግል ኩባንያዎች ወደ እኛ እንዲመጡ እና በሕጋዊ መንገድ ግዴታ እና ሙሉ ኃላፊነት ከምንወስድ የጽዳት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች መጥተው አገልግሎት እንዲያገኙ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

**ንግድና ልማት:** አመሰግናለሁ፤

**አቶ እክሊሉ:** እኔም በጣም አመሰግናለሁ፤እግዚአብሔር ይስጥልኝ።

# የኢትዮጵያ ቱሪዝም ዘርፍ እድሎችና ተግዳሮቶች



በቅርቡ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍን አስመልክቶ ብሄራዊ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ የምክክር መድረክ በአዲስ አበባ ተካሄዷል፡፡ በዚህ የምክክር መድረክ ላይ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍን አስመክቶ የፖሊሲ ምልከታዎችና ምክረ ሀሳቦች በሰፊው ተነስተዋል፡፡ በዚህ ጸሁፍ የቱሪዝም ዘርፍ ከፖሊሲ አንጻር እንዴት ይታያል ምን አይነት የፖሊሲ ድጋፍ ያስፈልገዋል፤የግሉ ዘርፍ ሚና ምን መሆን አለበት የሚሉ ርእሰ ጉዳዮችን እናስቃኛለን፡፡

የኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ዕምቅ አቅም ያለው ቢሆንም ዘርፉ ገቢ በማመንጨትና የአገሪቱን ገጽታ በመገንባት ረገድ ካለው አቅም አንጻር በበበቂ መጠን ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡ ይህንን ክፍተት ለመሙላት የተለያዩ ችግሮችን መፍታት ግድ ይላል፡፡ “ለቱሪዝም ዘርፍ ልማት እንደ መመሪያ የሚያገለግል አጠቃላይ ዕቅድ አውጥቶ ለማስተግበር ወይም በመደበኛ የዕቅድ አወጣጥና ውክልና አሰጣጥ ሂደቶች ላይ የተመሰረቱ የጋራ መርሆዎችን እንደ መስፈርት ለመጠቀም የሚደረጉ ሙከራዎች፤ አስቸጋሪና ውስብስብ የልማት ሁኔታዎች ላሉባቸው አውዶች የማይመጥኑ እንዲሁም በተለይ በማደግ ላይ ለሚገኙ አገራት የቱሪዝም መዳረሻዎች ፍላጎቶች የማይስማሙ ናቸው በማለት በቱሪዝም ዙርያ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ጥናት በሌላ በኩል ደግሞ፤ ከዘርፉ ከዕለት ከዕለት ተግባራዊ እንቅስቃሴና አሰራር ጋር በተያያዘ በቱሪዝሙ ዘርፍ ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች መካከልም በሚገባ የሰለጠነና ክህሎት ያዳበረ በቂ የሰው ሃይል አለመኖር፣ በቱሪዝም መዳረሻዎች የመረጃ ማዕከላት አለመኖር፣ ለቱሪዝም መዳረሻዎች የሚሰሩ የፕሮሞሽንና የማርኬቲንግ ስራዎች ደካማ መሆን እንዲሁም የመሰረተ ልማት አውታሮች አለመስፋፋት እንደ ዋና ዋና ተግዳሮቶች በባለ ድርሻ አካላት ተቀምጠዋል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ የአስጎብኝዎች ማህበራት አለመጠናከር፣ በዘርፉ በተሰማሩ አካላት መካከል ያለው ትስስር ወይም ግንኙነት የላላ መሆን፣ የማረፊያና የሌሎች አገልግሎቶች አቅርቦት እጥረትና አመቺ አለመሆን እንዲሁም የጸጥታና ደህንነት ችግሮችም ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች ባልተናነሰ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች መሆናቸውን በቱሪዝም ዙርያ ትኩረታቸውን ያደረጉ የጥናት ውጤቶች ያሳያሉ፡፡

የኢትዮጵያ ቱሪዝም የሚገኝበትን ደረጃ ለመፈተሽ በዘርፉ የሚከናወኑ ስራዎች የሚመሩባቸውን ስትራቴጂካዊ ሰነዶችና የሕግ ማዕቀፎች፣ የዘርፉን የቁጥርና አጠቃላይ መረጃዎች እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን የአፈጻጸም አቅምና ብቃት በዋናነት ትኩረት ሰጥቶ መገምገም እንደሚያስፈልግ የፖሊሲ ምልከታዎች ያሳያሉ፡፡ ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ገበያ የቱሪስት ምንጭ የሆኑ አገራት ትንተናም ዘርፉ የሚገኝበትን ደረጃ ወይም አጠቃላይ ሁኔታ ሊያመለክተን የሚችል ተጨማሪ ጉዳይ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ቱሪዝም በተለያዩ ተግዳሮቶችና ማነቆዎች የተተበተበ ቢሆንም ከሁሉም በላይ የዘርፉ መገለጫ የሆነው ዋነኛው ችግር ግን የዘርፉን የዕድገት ዕድል እንዲሁም በዘርፉ የሚከናወኑ ስራዎችን አስተዳደር የሚያመለክቱ ስትራቴጂካዊ ሰነዶች አለመኖር እንደሆነ የምርምር ስራዎች ያሳያሉ፡፡ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር የተቋቋመው የመንግስት አስፈጻሚ አካላት መቋቋማቸውን በሚገልጸው አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 4፣ 1995) መሰረት ነው፡፡ እ.ኤ.አ በ2009 የወጣው የቱሪዝም ፖሊሲም በኢትዮጵያ የቱሪዝም ዘርፍ ውስጥ በጉልህ የሚጠቀስ ተጨማሪ ስትራቴጂካዊ ሰነድ ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ የዱር እንስሳት ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅም ከአገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚጠቀስ ሌላኛው ጉልህ ሰነድ ነው፡፡

ያም ሆኖ ግን፣ ይህን መሰሉን ሰፊ እና የተለየ ዘርፍ ለማስተዳደር የሚያስችሉ ሰነዶች በበቂ መጠን ካለመኖራቸው በተጨማሪ መሰል ሰነዶች እርስ በእርስ የማይናበቡ መሆናቸውም የአገሪቱ የቱሪዝም ዘርፍ የሚገኝበትን ደረጃ የሚያመለክት ነው፡፡ ይህም በመሆኑ፣ በቱሪስት መዳረሻዎች የሚከናወኑ ስራዎች በዘፈቀደ የሚሰሩና አቅጣጫ ያልተበጀላቸው እንዲሁም የዘርፉን አላማዎችና ግቦች ያላማከሉ መሆናቸው በቅርቡ በተደረገው የግሉና የመንግስት የትብብር መድረክ ላይ ተገልጿል፡፡

እ.ኤ.አ በ2018 ለአገሪቱ ኢኮኖሚ 7.4 ቢሊዮን ዶላር ገቢ (በ2017 ከነበረው የ2.2 ቢሊዮን ዶላር ጭማሪ አስመዝግቧል) ያስገኘው የቱሪዝሙ መስክ የሚተዳደርባቸውና የሚመራባቸው ሕጋዊ ሰነዶችና አዋጆች ከላይ የተጠቀሱት እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ የቱሪዝሙ ዘርፍ በአሁኑ ወቅት ከአገሪቱ አጠቃላይ ኢኮኖሚ የ9.4 በመቶ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡

ከኢትዮጵያ ቱሪዝም የቁጥርና አጠቃላይ መረጃዎች ጋር በተያያዘ ከሚታዩ ችግሮች መካከል ተአማኒነት ያለው መረጃ አለመኖር፣ የተማለከ የመረጃ ማዕከል አለመኖር እና ከአገሪቱ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች ጋር በተያያዘ የተዛቡ መረጃዎች መኖራቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ መረጃዎች በየጊዜው በተገቢው መንገድ የሚሻሻሉ አለመሆናቸውም በዘርፉ የሚደረገው እንቅስቃሴ በበጎ አይን እንዳይታይ በር ሲከፍት እንደነበር ተስተውሏል፡፡ የቱሪዝም ሚኒስቴር መቋቋሙ እንዲሁም ለዘርፉ የ10 አመት ዕቅድ መውጣቱና የስራ ፈጠራ ስትራቴጂካዊ ሰነድ መዘጋጀቱ፣ በአገሪቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቱሪዝም ዘርፍ የተሰጠውን ትኩረት ማመላከቱን ያሳያል፡፡ ያም ሆኖ ግን፤ አሁንም ቢሆን አጠቃላይ የፖሊሲ አቅጣጫ ማስመቀጥን እንዲሁም ተገቢነት ያላቸው የሕግ ማዕቀፎች ማውጣትና ተቋማዊ ስርዓት መዘርጋትን ግድ የሚሉ ክፍተቶች አሉ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ በመላ አገሪቱ በቱሪዝሙ ዘርፍ የሚከናወኑ ስራዎች የሚመሩባቸውን የአሰራር ብቃት መመዘኛ ደረጃዎችንና ስርዓቶችን አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ የቱሪስቶችንም ሆነ በዘርፉ የተሰማሩ አካላትን እርካታ ማረጋገጥም ያስፈልጋል፡፡ በዘርፉ የሰው ሃይል ስልጠና፣ ልማትና አመራር ማስፋፋት የስራ አፈጻጸም አቅምና ብቃትን ከማሳደግ አንጻር ባለፉት አመታት በአንጻራዊነት የተሻለ ትኩረት እንደተሰጠው በምክክር መድረኩ ወቅት ተነግሯል፡፡

በዚህ የግሉ ዘርፍና የመንግስት የምክክር መድረክ ወቅት የኢትዮጵያን ቱሪዘም አስመክልቶ በርካታ ተግዳሮቶች ተነስተዋል፡፡ እንደ አጠቃላይ በቱሪዝሙ ዘርፍ እንዲሁም በተለይ በአስጎብኝዎች ላይ ተጽዕኖ የሚፈጥሩ የተለያዩ ዋና ዋና ተግዳሮቶች እንዳሉ በጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ በዘርፉ ላይ ያስከተለው ጫና፣ ከቀረጥ ነጻ ከሚገቡ ተሽከርካሪዎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ የግብር ህግና የኦዲት አሰራር እንዲሁም ዘርፉን እንደ ወጪ ንግድ ዘርፍ ተመልክቶ ትኩረት መስጠት፣ ከመሰረተ ልማት አውታሮች ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ የቱሪስት መዳረሻዎች ከደረጃ በታች መሆን እንዲሁም በብሔራዊ እና በክልል ደረጃ በሚከናወኑ የቱሪዝም እንቅስቃሴዎች መካከል ያለው መናበብ አነስተኛ መሆን እንደተግዳሮት የተጠቀሱ ጉዳዮች እንደሆኑ በምክክር መድረኩ ላይ ቀርበዋል፡፡

ከዚህም ባለፈ የቱሪዝሙ ዘርፍ ለኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከሚያስገኙ ዋነኛ ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ ዘርፉ ባለፉት አምስት አመታት በየአመቱ በአማካይ የ2 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ማስገኘቱን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ሁሉም የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች እንዲሁም የአሰራር መመሪያዎች ዘርፉ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ አሳንሰው የሚያዩና ተገቢውን ትኩረት የማይሰጡ ናቸው፡፡ ይህን ችግር የመፍታት ጥረት የሚጀምረው፣ ዘርፉ አገልግሎትን ለወጪ ንግድ የሚያቀርብ እንደሆነ አምኖ በመቀበልና እውቅና መስጠት እንደሆነ በመድረኩ ላይ ተብራርቷል፡፡ ከዚህ ባሻገርም ዘርፉ የግብር እፎይታ፣ የተለያዩ የጉዞና አስጎብኝ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ከቀረጥ ነጻ ማስገባትን ጨምሮ ለወጪ ንግድ ዘርፎች ከተሰጡ ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ይገባል በማለት የዘርፉ ተዋንያን በምክክር መድረኩ ላይ ሀሳባቸውን አካፍለዋል፡፡

በቱሪዝሙ ዘርፍ የሚታየው የመሰረተ ልማት ችግር እጅግ የከፋ እንደሆነ ቀርቧል፡፡ የቱሪስት ስፍራዎች፣ ወደ ቱሪስት መዳረሻዎች የሚወስዱ መንገዶች፣ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪዎችና ሌሎች ጉዳዮች እንደ አጠቃላይ በቂ ትኩረት አልተሰጣቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ እና ባሌ ብሔራዊ ፓርክ በዙሪያቸው የሚገኙ ነዋሪዎች በሚያደርጉባቸው ጣልቃ ገብነት ሳቢያ የሚገኙበት የከፋ ሁኔታ ቱሪስቶችን የሚያሸሽ እንደሆነ በቀረበው የፖሊሲ ምክረ ሀሳብ ላይ ተመላክቷል፡፡ ለዚህም ነው ፓርኮቹን የሚጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በመቀነስ ላይ የሚገኘው፡፡ በ2005 ላይ 5300 የነበረው የጎብኝዎች ቁጥር በ2007 ወደ 20500 ቢያድግም፣ ከ2010 አንስቶ ግን የጎብኝዎች ቁጥር ቅናሽ

ወደ ገጽ 8 የዞረ

# የኢትዮጵያ ቱሪዝም ዘርፍ...

ከ ገጽ 7 የዞረ

ማሳየት የጀመረ ሲሆን በ2017 ላይ 7600 ደርሷል።

በአገሪቱ ታሪክ ከፍተኛው የቱሪስቶች ቁጥር የተመዘገበው በ2017 ሲሆን፣ በአመቱ 933,000 ያህል ቱሪስቶች አገሪቱን እንደጎበኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በኤፍ ጂ ዲ ምላሻቸውን የሰጡ ተሳታፊዎች ግን የዚህን መረጃ ትክክለኛነት እንደማያምኑበት በቀረበው የፖሊሲ ምልከታ ላይ ታይቷል።

ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ለንግድ ወይም ለሌላ ጉዳይ ሆኖ ሳለ የቱሪስት ቪዛ ይዘው የሚገቡ ወይም አዲስ አበባ ቦሌ አለማቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያ ሲደርሱ የቱሪስት ቪዛ የሚጠይቁ ሰዎችን ማየት የተመለደ ክስተት መሆኑን የኢትዮጵያ አስገብኝዎች ማህበር ባሰራው ጥናት ላይ ተመላክቷል። ይህን መሰሉ የቱሪስት መረጃ አሰባሰብ ትክክለኛውን የቱሪዝም ገጽታ ለመገንዘብም ሆነ ለዘርፉ ውጤታማ ዕቅድ ለማውጣት ክፍተት እየፈጠረ እንደሚገኝ ታውቋል።
በዚህ የምክክር መድረክ ላይ በኢትዮጵያ አስተማማኝ ሰላምን በመፍጠር የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን እድልና እምቅ ሀብት መጠቀም እንደሚቻል ተገልጿል።

# የአዲስ ቻምበር ዋና ፀኃፊ አቶ ሺበሺ ቤተማርያም የኬንያ አምራቾች ማህበር አባላትን ተቀብለው አነጋገሩ...

ከ ገጽ 1 የዞረ

ንግድ ምክር ቤታቸው አንገብጋቢና ወቅታዊ የንግድ ማህበረሰብ ጥያቄዎችን በመለየትና ወርክሾፕ ፣ ጉባኤ፣ ሴሚናሮች በማዘጋጀት እና ውይይት በማድረግ የግሉን ዘርፍ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የፖሊሲ አድቮኬሲ ስራ እየሰራ ይገኛል ብለዋል ። አክለውም አዲስ ቻምበር ለኢትዮጵያ አክሲዮን ኩባንያዎችና ለካፒታል ገበያ ዳይሬክተሮች ጥቅም ሊሰጥ የሚችል የኢትዮጵያ ዳይሬክተሮች ኢንስቲትዩት መመስረቱን ተናግረዋል ።

ይህም አንዱ የምክር ቤቱ ጥንካሬ መገለጫ መሆኑን አንስተዋል። ለንግድ ማህበረሰብ እና ለኩባንያዎች መረጃ የሚሰጥ 24 ሰዓት የሚሰራ የሬዴዮ ፕሮግራም በስድስት ወራት ውስጥ ለመጀመር ንግድ ምክር ቤታቸው እንቅስቃሴ ላይ መሆኑንም ገልጸዋል።

ምክር ቤቱ የጨርቃ ጨርቅ ፣ ቆዳ ፣ አበባ ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፎችን በመለየት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑንም ለልኡካን ቡድኑ አስረድተዋል።

በቀጣይ አመት የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጠና ላይ ያተኮረ ንግድ ትርዒት በአፍሪካ ከሚገኙ ከተሞች መካከል በአንዷ ለማካሄድ ንግድ ምክር ቤቱ መወጠኑን ተናግረዋል ።

የኬኒያ አምራቾች ማህበር (Kenyan Association of Manufacturers) ዋና ኦፊሰር ቶብያዝ ኦላንዶ በበኩላቸው አዲስ አበባ የመጣነው በሁለቱ አገራት የንግድ ማህበረሰብ መካከል ያለውን ትስስር ለማጠናከር መሆኑን ለአዲስ ቻምበር ሚዲያ ገልፀዋል። የሉዑካን ቡድኑ ከአዲስ ቻምበር ዋና ፀሀፊ አቶ ሺበሺ ጋር ባደረገው ውይይት ምክር ቤቱ በርካታ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ተገንዝቧል ብለዋል ።

በተለይ የፖሊሲ አድቮኬሲ ላይ አዲስ ቻምበር እየሰራ ያለው ስራ አንዱ ጥንካሬ መሆኑን የጠቀሱ ሲሆን የንግድ ማህበረሰቡን ታሳቢ ያደረገ የሬዲዮ ፕሮግራም ያለው መሆኑና በቀጣይም 24 ሰዓት የሚሰራ የሬዲዮ ፕሮግራም ሊጀምር መሆኑን መስማታቸው እንዳስደነቃቸው ሚስተር ቶብያስ ገልፀዋል ።

የኬኒያ ንግድ ምክር ቤት የሚዲያ ልምድ የለውም ያሉት ሚስተር ቶብያስ ይህንን ከአዲስ ቻምበር የምንወሰደውና በሀገራችን የምንተገብረው መልካም ተሞክሮ ነው ብለዋል ።

በኢነርጂ አስተዳደር ፤ ጥበቃ እና አጠቃቀም ረገድ ያለው ተሞክሮ ምን ይመስላል የሚለውን ተሞክሮ እንዲመለከት የንግድ ምክር ቤቱ አመራሮች ኬኒያን እንዲጎበኙ ጥሪ አቅርበዋል ።



# Addis Chamber Training Institute (ACTI)

## List of July & August 2023 Training Programs

| No. | Training Topic | Delivery Date | Time | Training Fee | | Venue | Remark |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | Member | Non-Member. | | |
| 1 | International Financial Reporting Standards (IFRS) | July 24-28, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| | Aug. 21-Sept. 8, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 8,625 | 10,350 | ACTI | 15 half days | 5 half days |
| 2 | Project Management | July 31 - Aug. 4, 2023 | 1:30P.M-5:30P.M | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| | August 21-25, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days | 15 half days |
| 3 | Records Management | Aug. 28-Sept. 1, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 4 | Taxation in Ethiopia | September 4-8, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 5 | Human Resource Management | September 5-7, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 6 | Office Operations Management | September 18-22, 2023 | 8:30AM - 12:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 7 | Marketing Research | September 18-22, 2023 | 1:30PM - 5:30PM | 3,542 | 4,250 | ACTI | 5 half days |
| 8 | Supervisory Management | September 19 - 21, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |
| 9 | Digital Marketing | September 19 - 21, 2023 | 8:30AM - 5:30PM | 8,591 | 10,309 | Hotel | 3 full days |

**For further information, please contact the Training Institute through 011-551-3882, 011-551-8055 ext. 229, 0911194965, 0911343078, dejedesalegn@gmail.com and hiwottlhn9@gmail.com**

# የሴቶች ፈተና በሥራ ቦታ ...




- የጾታዊ ጥቃቶች መከላከያ እና ምላሽ ብሔራዊ ፖሊሲ ረቂቅ ሆኖ ከርሟል
- አጥፊዎች ላይ የተጣለው ቅጣት እንዲከብድ ተጠይቋል፤

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**

በሴቶች ላይ ስለሚደርስባቸው የመብት ጥሰት ጉዳይ ብዙ ተብሏል፤ብዙ ተጽፏል ዛሬም በብዙ ሲነገር እንሰማለን። የሚደርስባቸው ጥቃት ከቤት ጀምሮ፤በትምህርት ቤቶች ፤በሌሎች ማሕበራዊ እና ኢኮሚያዊ ተሳትፎአቸው እንዲሁም በሥራ ገበታቸው ጭምር የተለያዩ አድልዎ፤ ጾታዊ ትንኮሳ አልፍ ሲልም በሃይ የታገዘ ጥቃቶች ይደርስባቸዋል። አሁን አሁን ላይ ከቀደመው ጊዜ ሁኔታው የመንግሥት እና መንግሥታዊ በሆኑ እና ባልሆኑ እንዲሁም በግል ኩባንያዎች ጭምር ባሉ በሥራ ቦታዎች አካባቢ የሥርዓተ ጾታ ክፍሎች ማየት እየተለመደ መጥቷል። በየጊዜው በመገናኛ ብዙኃን እና በትምህርት ቤቶች ወዘተ አማካኝነት በሴቶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች እና መከላከያ ዘዴዎችን አስመልክቶ ትምህርት ቤቶች ከአብዮቱ ወራት ጀምሮ ትምህርቶች ሲሰጡ እንደነበር ልብ ይሏል።

ይህ ሁሉ ትምህርት ተደማምሮ የሚያስተላልፈው መልእክት አንድ ጉዳይ ይመስላል። እርሱም በሴቶች ልጆቻችን ፤እህቶቻችን እና በእናቶቻችን ላይ በሴትነታቸው ምክንያት ብቻ ከሚደርስባቸው ጥቃት ለመከላከል እንዲቻል ተብሎ ነው።

በተለይ በሥራ አካባቢ ላይ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ወሲባዊ ትንኮሳዎች እና ጥቃቶች እየቀነሱ እንደሆነ የቅርብ ጊዜ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህ ማለት ግን ችግሩ የሴቶች በሥራ ቦታዎች ላይ ከሚደርስባቸው በደል ለመከላከል በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ለመወያየት ሰሞኑን የአዲስ ቻምበር በጠራው የምክክር መድረክ ላይ ችግሩ ዛሬም ገና እንዳለ ተነግሯል።

የንግድ ም/ቤቱ ፕሬዝደንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በውይይቱ ላይ ባሰሙት ንግግር

ሴቶች በጾታቸው ብቻ ወደ ላይ ከፍ የማይሉበት ሁኔታ አለ፤ ከወንዶች ጋር በእኩል የማይታዩበት ሁኔታዎች አሁንም በየሥራ ቦታዎች ይስተዋላሉ ብለዋል። በሥራ ቦታ ላይ ብቃት እና ውጤታማ ሁኖ መገኘት ትልቁ መመዘኛ መሆን እንዳለበት እና ሴት በመሆናቸው ብቻ በተለያዩ ዘዴዎች ሴቶች ላይ ማንኛውም በደል ሊፈጸምባቸው አይገባም ብለዋል።

መንግሥት ሴቶችን ከጥቃት ለመከላከልና መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ ጥረቶች እየደረገ ነው። ከጥቂት አመታት ወዲህ የታወጁት የቤተሰብ፤ የሠራተኞች እና የሲቪል ሰርቪስ የመሳሰሉት አዋጆች የሴቶችን ማሕበራዊ፤ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች እና ጥቅሞች ከማስጠበቅ አንጻር ውጤት አስገኝተዋል። በሕብረተሰቡ ዘንድ የአስተሳሰብ ለውጥም እየመጣ ነው ብለዋል።

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ሴቶች በሥራ ገበታቸው ላይ እያሉ ጾታ-ተኮር ጥቃቶች እየተፈጸሙባቸው እንደሆነ በየጊዜው ይሰማል ። በተለይ ሴቶች በሚበዙበት አንደ ጨርቃጨርቅ እና ሰፋፊ እርሻዎች ባሉ የሥራ ቦታዎች በሴቶች ላይ የተለያዩ ጥቃቶች ይፈጸምባቸዋል።

ይህንን አሳሳቢ ጉዳይ የአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት አንስቶ ለንግዱ ሕብረተሰብ የተለያዩ ትምህርታዊ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች እየሰጠ ነው ብለዋል። በተለይ በምክር ቤቱ አባል ኩባንያዎች ዘንድ የሴቶች የሥራ አካባቢ መብት አጠባበቅ እና እንክብካቤ አስመልክቶ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎች እየሰጠ ነው ሲሉ ፕሬዝደንቷ ገልጸዋል፡ አሁንም ቢሆን ሴቶች በሥራ ገበታቸው ላይ እያሉ ጾታ-ተኮር ጥቃቶች እየተፈጸሙባቸው እንደሆነ በየጊዜው የሚወጡ መረጃዎች ያስተጋባሉ።

በአገራች ተጨባጭ ሁኔታ ሴቶች በሥራ ቦታ ላይ ጥቃት ከሚስተዋሉባው የሥራ ዘርፎች መካከል ሴቶች በብዛት የሚሳተፉባቸው ማለትም እንደ አበባ እርሻዎች፤ኢንዱስትሪ ፓርኮች፤ሰፋፊ እርሻዎች በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቅርብ ጊዜ ጥናት እንደሚያሳየው በአንዳንድ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ በሴት ሰራተኞች ላይ የተለያዩ አይነት ጾታ ተኮር ጥቃቶች እንደሚደርሱ አሳይታል። ከቅጥር ጀምሮ፤በደመወዝ እና የደረጃ ዕድገት ክልከላዎች፤ እና ሌሎች ጾታዊ ጥቃቶች ይፈጸምባቸዋል።

ይኸው ችግር በብዙ ወጣት ሴት ሠራተኞች የሚደርሰው ችግር እንዲቀጥል ካስቻላቸው ምክንያቶች አንዱ በአጥፊ ወንዶች ላይ የፍትሕ አካላት ጠንካራ ቅጣት ባለመውሰዳቸው ነው ይላል። በተመሳሳይ ሰፊ የሴት ሰራተኞች ቁጥር የሚታይባቸው የሥራ ገበታዎች የአበባ እርሻዎች ናቸው።

እዚህ ላይ በኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ማሕበር የተሰራው ሥራ በመልካም ተሞክሮነቱ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ወደ 65 በሚጠጉ የአበባ እርሻዎች ተቀጥረው የሚሠሩ ሴቶች ቁጥራቸው ከ200 ሺ በላይ ይሆናል። ማሕበሩ አንድ ወጥ የሴት ሠራተኞች ጥበቃ እና ደህንነት ፖሊሲ አዘጋጅቶ በአባላቱ እንዲተገበር እያደረገ ነው። እንዲሁም በእያንዳንዱ እርሻ ጣቢያ የሴቶችን መብት እና ጥበቃ የሚከታተሉ ኮሚቴዎች ተቋቁመው ቁጥጥር እያደረጉ ነው፤

ከኢት/ያ ሆርቲካልቸር አምራቾች እና ላኪዎች ማሕበር ተወክለው የመጡት ወ/ሮ ዮዲት ግርማ በእያንዳንዱ የእርሻ ጣቢያ የሴቶች ጥበቃ እና ደህንነት እንዲሁም ጥቃትን ለመከላከል የሚረዳ ፖሊሲ ማሕበራቸው አዘጋጅቶች ስልጠና ሰጥቶ እና ተቆጣጣሪ ኮሚቴዎችን አቋቁሞ ክትትል እየደረገ መሆኑን በማብራራት ተሞክሮአቸውን ለሌሎች ባለድርሻዎች አካፍለዋል።

በመንግሥት በኩል ለችግሩ ምላሽ ለመስጠት ተቋማዊ እና ሕጋዊ ሥርዓቶችን አበጅቶ እና አደረጃጀቶችን ፈጥሮ እንቅስቃሴ እያደረገ አንደሆነ ይታወቃል። ነገር ግን በአገር ደረጃ በአጠቃላይ ጾታዊ ጥበቃ እና ምላሽ መስጠት የሚያስችል ወጥ የሆነ ፖሊሲ አለመኖሩ ችግሩን በቀላሉ መግታት እንዳይቻል አድርጎታል በሚል የቀረቡ ጥናቶች መንግሥትን ይወቀሳሉ። ከሴቶች እና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ተወካይ የሆኑት ወ/ሮ ሕሊና ላቀው በበኩላቸው የሴቶችን የሥራ ቦታ ላይ ከጥቃት የሚከላከል ፖሊሲ መ/ቤታቸው አዘጋጅቶ ረቂቁን ለፕላንና ልማት ኮሚሽን ማቅረቡን ገልጸዋል። ነገር ግን ፖሊሲው አዲስ በተጀመረው አሰራር መሠረት መንግሥታዊ ፖሊሲዎች በፕላንና ልማት ኮሚሽን ታይቶ እንዲጸድቅ በመወሰኑ የኮሚሽኑን ምላሽ በመጠባበቅ ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል። ነገር ግን የጾታዊ ጥቃት ጥበቃ እና ምላሽ ብሔራዊ ረቂቅ ፖሊሲ ጸድቆ እንደመጣ መ/ቤታቸው ለመተግበር ዝግጁ ነው ብለዋል።

በዝግጅቱ ላይ ከዴንማርክ ኢንዱስትሪዎች ኮንፌዴራሲዮን የመጡት ክላራ ሃልቮርሰን በአገራቸው ስላለው የሴቶች ማሕበራዊ፤ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መብቶ አጠባበቅ ሥርዓት ዙሪያ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በተለይ በግል ኩባንያዎች ዘንድ የሴቶች የሥራ ላይ መብቶች እና ጥበቃ አስተማማኝ እና ዘላቂ እንዲሆን የኩባንያ ባለቤቶች ገገር የሆነ የቃልኪ ዳን ሰነድ ይፈርማሉ።

በአገሪቱ ለሴቶች መብት እና ጥበቃ የወጡ የተለያዩ ሕግጋት አሉ። ነገር ግን ይህ ኮንፌዴራሲዮን የሚያስተገብረው እና የሚከታተለው የቃልኪዳን ሕግ ሴቶች በሥራ ላይ በራሳቸው እንዲተማመኑ እና አሰተዳደራዊ አድልዎ እንዳይደርስባቸው ዋስትና የሚሰጥ ነው ሲሉ ያገራቸውን ተሞክሮ አካፍለዋል።

# የግንባታው ኢንዱስትሪና ተግዳሮቶቹ በኢትዮጵያ




**በስታፍ ሪፖርተር**

ኢትዮጵያ በአፈሪቃ በህዝቦቿ ቁጥር ከናይጄሪያ ቀጥላ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ ከ110 ሚሊዮን ህዝብ በላይ እንዳላት የሚነገርላት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የህዘብ ቁጥር እድገት ምጣኔ ከሚታይባቸው የአለማችን ሀገራት ተርታ ትመደባለች፡፡ ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር እና የከተሜነት መስፋፋት እንደ መኖርያ ቤት የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶችን፣የስራ እድልን እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማዳረስ ትልቅ ፈተና ሆኗል፡፡ በቅርብ የወጡ መረጃዎች እንደሚያሳዩት በኢትዮጵያ የከተሜነት እድገት በአመት በ4.7 በመቶ እያደገ እንደሆነ እና 21 በመቶ የሚሆነው ህዘብ ደግሞ በገጠር የሚኖር ሲሆን ይህ አሀዝ በአፍሪቃ ከሰሀራ በታች ያሉ ሀገራት የከተሜነት መጠን ጋር ሲነጻጾር የሀያ በመቶ ቅናሽ ያሳያል፡፡ እንደ መዲናይቱ አዲስ አበባ የመሳሰሉ ከተሞችን ስንመለከት ደግሞ የህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የመጣበት እና እንደ መኖርያ ቤት የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ለማዳረስ ትልቅ ፈተና የሆነበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በኢኮኖሚው ረገድ እንደ አለም ባንክ የቅርብ መረጃ ከሆነ በባለፉት ሁለት አስርት አመታት ውስጥ የግንባታው አገልግሎት በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል፡፡ ለዚህም በዋናነት ይህ ዘርፍ በመንግስት ድጋፍ ማግኘቱ ሲሆን ከባለፉት 15 አመት አንስቶ መንግስት የቤት ልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የቤት ፍላጎትን ለማማላት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ ባለፈ የግሉ ዘርፍ በግንባታው ኢንዱስትሪ ውስጥ በስፋት እንዲሰማራ መደረጉ ወሳኝ የሆነውን የመኖርያ ቤት ጥያቄ በመመለስ ረገድ ፋይዳው ብዙ ነው፡፡ እንደዛም ሆኖ ግን የግንባታው ኢንዱስትሪ እንደ ቤት ፍላጎት የመሳሰሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ሊመልስ አልቻለም፡፡ በተለይም ደግሞ ፈጣን የከተሜነትና የከተማ መስፋፋትን ተከትሎ የሚመጣውን የቤት ፍላጎት ለመመለስ ከፍተኛ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል፡፡ በኢትዮጵያ በግንባታው ዘርፍ ውስጥ የግሉ ዘርፍ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ለበርካቶች የስራ እድልን ከመፍጠር አንስቶ እስከ ቤት ፍላጎትን እስከ መመለስ ድረስ የግሉ ዘርፍ አስተዋጾ ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ኢትዮጵያ በሥነ-ሕንጻ ቅድመ ታሪክ ያላት አገር ናት፡፡ ቅድመና ታላቅ እንደመሆኑ ዘርፉ ሰፊና ትልቅ ሚና አለው በአለም ኢኮኖሚ ላይ፡፡ የአለምአቀፍ መረጃዎችን ስንመለከት ኮንስትራክሽ 10.8 በመቶ GDPን ይሸፍናል፡፡ በአለም ላይ የገበያ መጠኑ 10 ትሪሊየን የአሜሪካ ዶላር ነው፡፡ በሀገራችን ደረጃም ከግብርና በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጧል፡፡ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃነት የሰው ሃይል ቀጣሪ ነው፡፡ ከአገሪቷ ሶስቱ ዋነኛ የኢኮኖሚ ዘርፎች አንደኛው ነው፡፡ የአንድ ሀገር የኮንስትራክሽን እንቅስቃሴ እና የሀገር ኢኮኖሚ እድገት በአንድነት የሚታይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ 30% GDP በ Growth fixed Capital formatiom (GFCF) በሥነ-ሕንጻ መዋዕለ ንዋይ ላይ አፍስሳለች፡፡ በዚህም የተነሳ በሚቀጥሉት አስርት ዓመታት በአገሪቷ ላይ ኮንስትራክሽን በአግባቡ ድጋፍ ካገኘ የማደግ እድሉ ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል፡፡

አገራችን በ2030 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለመሰለፍ በሚደረገው ራዕይ እና ጥረት የግንባታው ዘርፍ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የግሉ ዘርፍ በዚህ ረገድ በኮንስትራክሽንና በኢኮኖሚያዊ እድገት የማይተካ ቦታ አለው፡፡ በአፍሪካ የኮንስትራክሽን ግብይት ትልቅ ድርሻ እንዲኖራት ኢትዮጵያ እንደመፈለጓ ዘርፉ ከፍተኛ እድል አለው፡፡ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ለኢኮኖሚ እድገት ዋና አንቀሳቃሽ ሀይል ተደርጎ የሚታሰብ ነው፡፡ ነገር ግን ዘርፉ ለብሔራዊ ልማት ያለውን እምቅ ድርሻና ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅዖ እንዳይወጣ የሚያደርጉ ብዙ ተግዳሮቶችና እክሎች አሉበት፡፡ ለብዙ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ ቴክኒካዊ ችግሮች የተጋለጠ ነው፡፡ የኢንዱስትሪው ስኬታማ ሆኖ መፈጸምን ጥያቄ ውስጥ የሚከቱ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ በአጠቃላይ በዘርፉ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ስንመለከት አገራችን ካለባት የዘርፉ ችግሮች ላይ በዓለም ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች ተመሳሳይ መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከነዚህም ውስጥ የኮንስትራክሽን መዘግየት፣ የፖሊሲ አፈጻጸም እና ሙስና የኮንስትራክሽን ተቋራጮች እና አማካሪዎች አቅም ውስንነት፣ የቅንጅት እና የመገለጫ አለመኖር፣ የደረጃ መለኪያ አለመቀመጥ ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህም ባለፈ በአሁኑ ወቅት በአለምአቀፍና በሀገር ውስጥ ግልጽነት በጎደለው ንግድ ምክንያት የተከሰተው የግንባታ ግብአት እጥረት በበርካታ አልሚዎች ላይ ከፍተኛ ጫናን እየፈጠረ እንደሆነ በግንባታው ዘርፍ ላይ የተሰማሩ አልሚዎች ሲናገሩ ይደመጣል፡፡

በተለይም በባለፉት ሁለትና ሶስት አመታት ውስጥ በመከሰቱ የግንባታ ፕሮጀክቶች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የተቃረጡበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በዚህም የተነሳ ታዲያ የግንባታ ውሎች መቋረጥ አንስቶ በግንበታ ዘርፍ ውስጥ ተቀጥረው ሲሰሩ የነበሩ ዜጎች ስራ አጥ መሆን ይጠቀሳሉ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም በዚህ አካሄድ በኢትዮያ ያለው የቤት ፍላጎትና አቅርቦት በአጭር ጊዜ የሚመለስ አይደለም አይደለም የሚሉ በርካታ ሀሳቦች ሲሰነዘሩ ይደመጣል፡፡ አሁን ላይ የሚስተዋለው የሲሚንቶ እጥረት ከተቀረፈ እና ጠንክሮ መስራት ከተቻል የግንባታ ኢንዱትሪን ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሳደግ እንደሚቻል በዚህ ዘርፍ ውስጥ የተሰማሩት ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ የቤት ፈላጊ ሰዎች ቁጥር ከፍተኛ በሆነባት ኢትዮጵያ ብቃት ያለው የግንባታ ኢንቨስትመንትን መፍጠርና ቀጣይነት ያለው የመንግስት ድጋፍ ዋናው መፍትሄ ሲሆን እንደሚችል የዘርፉ ባለሙያዎች ምክረሀሳባቸውን ይሰነዝራሉ፡፡ መንግስት በግንባታው ዘርፍ የሚያደርገው እንቅስቃሴ መልካም ነው የሚሉት አቶ ዘነበ ነገር ግን አሁን ላይ የሚስተዋለው የቤት ችግር በመንግስት ብቻ የሚፈታ አይደለም ይልቁንስ የግሉ ዘርፍ በዚህ ዘርፍ በሰፊው ሊሰማራ ይገባዋል ብለዋል፡፡

በሩሲያና በዩክሬን መካከል ከወራት በፊት የተከሰተው ግጭት ኢኮኖሚያዊ አንደምታው ከፍተኛ ነው፡፡ የሁለቱ ሀገራት ጦርነት የአለምን የግብይት ሰንሰለት ክፉኛ ጎድቶታል፡፡ ከግብርና ምርት አንስቶ እስከ ነዳጅ እንዲሁም የግንባታ እቃዎች እጥረት ያስከተለው የሩሲያና የዩክሬይን ጦርነት ዳፋው ለኢትዮጵያም ጭምር እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሁለቱ ሀገራት ጦርነት ምክንያት ከተፈጠረው ችግር በተጨማሪም የመሬት አቅርቦት፣የኤልክትሪክ ሀይል አቅርቦት የመሳሰሉት አሁንም የግንባታው ዘርፍ ዋና ዋና ማነቆዎች እንደሆኑ ማስተዋል ይቻላል፡፡ እነዚህን ችግሮች በፍጥነት በመፍታት የቤት ፈላጊዎችን ችግር መመለስና የግንባታው ዘርፍ የሀገር ኢኮኖሚን በማነቃቃት እንዲሁም ተጨማሪ የስራ እድልን በመፍጠር ረገድ የሚኖረውን ሚና ማሳደግ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡

በዚህ በያዝነው ክፍለ ዘመን በተለይም በውጪው አለም አንድን ቤት በአጭር ጊዜ ውስጥና በአነስተኛ ወጪ መስራት በመቻሉ ዜጎች በቀላሉ የቤት ባለቤት ሲሆኑ ይስተዋላል፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት የሆነው በግንባታው ዘርፍ ያለውን የግንባታ ቴክኖሎጂ ማዘመን ሲሆን የቤት መስሪያ ግብአቶችን ከመደበኛው ግብአት ማለትም ከሲሚንቶና ድንጋይ ውጪ ያሉ አማራጮችን በመጠቀም በቀላሉና በአነስተኛ ወጪ የሚሰሩ ቤቶችን መገንባት አንዱና ዋናው ስትራቴጂ መሆን እንዳለበት በግንባታው ኢንዱስትሪ የተሰማሩ ዜጎች ሲናገሩ ይደመጣል፡፡ መንግስት አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ፣አዳዲስ የግንባታ ቴክኖሎጂዎች እንዲተዋወቁ መንግስት እገዛ ማድረግ አለበት፡፡ ከዚህም ባለፈ መንግስት አዳዲስ ቴኮኖሎጂዎች በቀላሉ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ምቹ ሁኔታን መፍጠር አለበት፡፡